ካለፈው የቀጠለ

- እንደምን ከረሙ እናቴ ? በሰላም ከረሙ ? ስራ በዝቶብኝ ሰሞኑን ጠፋሁ ።
- ምን ይሳካል ብለህ ። የውጭ አገር ኑሮ። እመለከተው የለ በሌሎቹ ።
- ለብርዱዋ ይህችን ይገፍ መጣሁሎት ። ጣይቱ ነው የሚሉዋት የዚህ አገር ልጆች ። በብርድ ጊዜ ከውስጥ የምትለበስ ሱሪ ነች ። ከጥጥ ነው የተሰራች። ይሞክሩዋት ። ያመሰግኑኛል ።
- እስቲ እሞክራታለሁ።እንደው የዛን ቀን ስንቱን አንስተን ተጫውትን ። ሁሉም ሳስበው ከረምኩ። መቼም የሚደንቅ ነው የድሮ ነገር።ለመሆኑ ለጓደኛህ ፃፍክልት ?
- አዎ ። ዕፌለታለሁ ። ከመለሰልኝ አይደል ? ምን ይታወቃል ምን እንደሚያስብ ። ለማንኛውም እንግዲህ መጠበቅ ነው ።
- ልጆቹ የሚሉት እረጅም ደብዳቤ ለብዙ ወራት ዕፎ ደብቆ ይዞአል ነው ። ሳንተ ነው የፃፊው ብለው ነግረውኛል ። ደብዳቤው እሳት ድምፅሽ ድምፄ ነው የሚለው ነው አሉ ። ማን አውቆት ማን አነበበውና ።
- ምንድነው የሚለው ደብዳቤው የሚሉኝ ?
- „እሳት ድምፅሽ ድምፄ“ ማን አነበበው ብልህ ? ከላይ ያለውን እንጂ ።
- አይ ጥሩ ስም ነው የሰጠው ። ማለፊያ ስም ። አያውቁዋትም ያችን ከኛ ቤት ጀርባ የነበሩ ልጅ ። በቀይ ሽብር መውጫው ለይ የጣሉዋት ። መቼም አይዘነጉዋትም ።
- እንዴት ብዬ ልጅ እንዴት ብዬ። እንዴት ልዘንጋት ። እኛ ቤት ትመጣ አልነበር ።
- አዎ አውቃለሁ ።
- ምን ብለህ ፃፍክለት ለመሆኑ ለጓደኛህ ።

ውድ ጓደኛዬ

“መኖር ከማንም ጋር ይኖራል ። መለያየትም እንደዚሁ ። በአዕምሮ ወስጥ የሚፃፍ ውድ ጓደኛ ማግኘት ግን ከማንኛውም የበለጠ ብሩህ ተስፋ ነው ።“ በዬ

- አይ ልጄ ልክ ነህ ።

ይኖራል እንጂ ልጄ ይኖራል
እንቢስ ተብሎስ ምን ይኮናል።

- አዎ እናቴ !!!!!

ከባንዳው፣ከቀጣፊው ፣
ከሆዳሙ፣ ከአድርባዩ
ከፋሽሽቱ፣ ከጨካኙ
ከማይረባው ከተልካሻው
ከከሀጁ ከአቃጣሪው

ይኖራል እንጂ እናቴ ይኖራል
እንቢስ ተብሎስ ምን ይኮናል።

- አይ ልጄ

ይሂንማ ለኔ ተወው
አውቀዋለሁ ህይወቴ ነው፡፡

ከባንዳው ነው ከቀጣፊው
ሁል ጊዜስ የምኖረው፡፡
የት ልገባ የት ልሂድ ነው
ከማይረባው ከተልካሻው።
ከሆዳሙ ከጉረኛው
ከዚህም ከዚያም ከሚመጣው።

- አውቅዋለሁ እንጂ እናቴ

ከኢንቬስተሩ ከዘናጩ
የሰው ቋንቋ ከሚቀናው
ከትጉሁ ከአሳማው
ሆዱን ብቻ ከሚያስበው።
ከዘረኛው ከጊዜው ሰው
ያታው በውል ከማይለየው።

ይኖራል እንጂ  ይኖራል
እንቢስ ተብሎስ ምን ይኮናል።

- የዛስ የጨካኝ ኑዛዜ እንዴት ነው ።
- ምነው ማወቅ ፈለጉ?
- ማን ጠልቶት ብለህ ?

- እንግዲህ ይኼውና በርትተው አንብቡት ።

- እስቲ መነፅሬን ስጭኝ አንቺ ቶሎ በይ ።

- ምነው ቸኮሉ ።

- ምነው አልቸኩል ልጄ።እናንተ ታሪካችሁም እየቆጠባችሁ እየፃፋችሁ ሳናውቀው እንሙት ብለህ?

- በሉ በርቱ እኔም ልሂድ ።

# የመጨረሻው ሰይጣን

**ከቤልጅግ አሊ**

**ካለፈው የቀጠለ**

ታሪኬ በፍቅርና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ነው ። ከህፃንነቴ ጀምሬ በሰዎች እንድወደድ እፈልግ ነበር ። ምንግዜም በሰዎች የተፈቀርኩ እንድሆን ምኞቴ ነበር  ። እያደር ግን እንድፈራና እንድከበር እፈልግ ጀመር ። ማንነቴን ለማረጋገጥ የወሰድኩት ጎዳና ወደ ጨካኝነት ሳይለውጠኝ በፊት የተከበርኩ ዜጋና የቤተሰብ አፍቃሪ ለመሆን እጥር ነበር ። ምንአልባት የህይወት ታሪኬን ስታነቡ በጣም ትጠሉኝ ይሆናል ። በልቤ ውስጥ ያለው ጠባሳ ለዘላላም እያቃጠለ ያንገበግበኛል ።ሁላችሁም ይህንን ታሪኬን ስታነቡ ምን አይነት ሰው ነው ማለታችሁ አይቀርም ። አውነቱን ልንገራችሁ ፡ በአለም ላይ ታላላቆቹ ጨካኞች እንኳን ሳይቀሩ አንድ ቀን ህፃን እነደነበሩ እና የእናት ፍቅር እንደሚያስፈልጋቸው ልትረዱት ይገባል ። ከዛሬ እኩለ ሌሊት ጀምሮ እንደ ሰው መኖሬ ያከትማል ። ይህ የመጨረሻ  ፅዋዬ ስለሆነ አብረን እናንሳ ። ካሁን በሆላ በዚህ አለም ለይ ምንም የምፈልገው ነገር የለም ። የምፈልገው ቢኖር አሁን እኔ ከሚሄድበት ቦታ አስቀድሜ የሰደድኳቸውን ሰዎች ማግኘት ነው ። የነርሱን ፍርድ እዛው እቀበለዋለሁ ። ትንኝ እንኳ አልገደልኩም ብዬ አልመፃደቅም ። ተግባሬ ከኔ በላይ ጎልቶ ስለሚታይ መደበቅ የሚቻልም አይሆንም ።ታሪኬን በአጋጣሚ ህይወቱን ላተረፍኩለት ግለስብ ፅፌ ትቻለሁ ። ስለማምነው በመሰለው ሰአት ከዛሬ እኩለ ሌሊት ጀምሬ ሊያወጣው ይችላል ።

ወድ ጓደኛዬ

የመጨረሻውን ደብዳቤ ፅፌ ስጨርስና አንተም ደብዳቤው ሲደርስህ ደውልልኝ በአልኩህ መሰረት ፡ ስትደውልልኝ ፤ አንተን አይግባህ እንጅ ይህ ስልክ በሕይወቴ የምጠብቀው የመጨረሻ ጥሪ ነበር ። እስከ ዛሬ በላክልን ገንዘብ ቃል በገባሁት መሰረት ምንም ሳላጓድል ቤተሰቤን ስረዳ ቆይቻለሁ ። ዛሬ ግን የራሴን ተስካር፤ ጉደኛ ነኝ እና፤ እራሴው ልበላው ተዘጋጅቻለሁ ። ድሮ ሰው ለመግረፍ ወይም ለመግድል በማስብበት ጊዜ እንደማደርገው ሁሉ ውስኪዬን ገዝቼ ጥሬ ስጋዬን አምጥቼ ተቀምጫለሁ ። ዛሬን ልዩ የሚያደርገው ቢኖር የምገርፈውም ሆነ የማሰቃየው ሰው አለመኖሩ ነው ። የሚኖረው ግን በጨካኝነቱ የታወቀውን ብቸኛውን ሰይጣን ለማጥፋት ነው ። ይህን በማድረግ ለብዙ ጊዜ የተሰቃየ ህይወቴን ለአንዴም ለሁሌም ወደ መጨረሻው መቃጠያ ቤቴ አወስደዋለሁ ። ለኔ ገሃነብ እሳት እንኳ ቦታ ይኖራል ብዬ አልጠብቅም። ሰው ነኝና መፍራቴ አልቀረም ። ይህንን ፍርሃት ድሮ ባውቀው ኖሮ፤ ምን ያህል በሌሎች ስቃይ ባልተደሰትኩ ነበር ።

እግዚሃብሄር ህይወታችንን ሲያገናኘው በምን እንደሆን በማላውቀው ነገር ያንተን ህይወት ያኔ እንደትገደል አደረግሁ። ይህ ጠባዬ አልነበረም ። ግን አንድ ነገር ጭንቀላቴ ወሰጥ መጣ ። ገና ከባላገር መጥቼ ሰፈር ስንገናኝ ነው የተስማማኸኝ ። ስለገጠር ማወቅ ትፈልግ ነበር ። ብዙም ትጠይቀኝ ነበር ። ስለገበሬዎቹ ኑሮ ማወቅ ትፈልግ ነበር ። እኔም አስረዳህ ነበር ። የገበሬዎቹ ህይወት ያሳዝናል መቀየር አለበት የምትለው ፡ የሰውን ችግር በሩቅ የመዳሰስ የመቻል ችሎታህ ያስገርመኝ ነበር።እኔ አብሬያቸው ኖሬ ያላየሁትን ሰቆቃቸውን አንተ ከኔ ሰምተህ እንዲያ ማዘንህ በልቤ ውስጥ ለአንተ ፍቅር አትርፎልኛል። ከሌሎቹ ሁሉ አንተ ስለምትቀርበኝ እኔም እቀርብህ ነበር ። ታዲአ አንድ ቀን ትምህርት ቤት ሌሎቹ „ፋራ“ „ፋራ“ ሲሉኝ አትበሉት ብልህ የተጣላኸው ትዝ ይለኛል ።ለሰው ምን ያህል እንደምትሞት ያወቅሁት ያኔ ነው ። አንተ በምትገረፍበት ጊዜ እንኳ እሌላ ክፍል ወስጥ ውስኪ እንጠጣ ነበር። ለአንተ ያለኝ ፍቅር እንኳ ጨካኝነቴን ሊለውጠው አልቻለም ። ግን ጥሩነትህን ስለማውቅ በሆላም ችግር እንደማትፈጥርብኝ በማወቅ እንድትገደል አልፈለግሁም። ማና አወቀው ታዲያ ህይወታችን እንደገና እንዲህ እንደሚተሳሰር።

ይህ የመጨረሻዬ ኑዛዝዬ ነው ። ሌሎች እንዲያነቡት የምታደርግ ከሆን አንድ ስም ስጠው ። የመጨረሻው ሰይጣን ነኝና የመጨረሻው ሰይጣን በልልኝ ። ዛሬ ጉዞዬን የጨረስኩ ይመስለኛል ። እንደኔው ገና መንገድ ላይ ለሆኑ ሰይጣኖች የምነግረው አለኝ ። ይህንን ምክሬን ተቀብለው ልባቸውን ካላፀዱ ምንም የሕየወት ደሰታ አያገኙም ። ያጠፋነው ጥፋት ትልቅ ነው ። ልንክደው አይገባም ። ምክንያትም መፈለግ አንችልም ። አኛም ጠፍተናል ። አገራችንን አጥፍተል ። ታሪካችንንም አጥፍተናል። ጨካኝነታችን ባለም እንዲታወቅ አድርገናል ። ይባስ ብለን የገደልናቸውን ብንወቅስ ምንኛ ከስዕብና የወጣን መሆናችንን ብቻ ነው የምናሳየው ። ሁላችሁም እንደኔው በውሰጣችሁ እደገደልናችው ፤እንደገረፍናቸው ፤ ንፁህ ልቦናና የተከበረ ስዕብና ይዘን ብንሞት እንደምንትፈልጉ የታወቀ ነው ። ግን ምንም ቢሆን የረፈደ ነገር የለም ፤ ዛሬም ቢሆን ንሰሐ መግባት ይቻላል ።

አንዱን እሱን ጓደኛዬን በማላውቀው መንገድ በማትረፌ ፤ የኔም ሆነ የቤተሰቦቹ ህይወት ተረፈ። ከገደልኳቸው ግማሹን እንኳ ባድን ኖሮ የስንት ሰዎች ህይወት ይድን ነበር ። ሁሉንም ብናድናቸው ኖሮ አገራችንም በዳነች ነበር ። ዛሬ የደረሰብን ውርደት እነርሱ ያኔ ያሉንን ባለመቀበላችን መሆኑን እንክዳለን ። መግደል መፍትሄ አለመሆኑን አሁንም ያልተገነዘብን እንኖር ይሆን። ይህንን ክደን በውሰጣችን አውነቱን እያወቅን ዛሬም እንደዛ ግዜ በትዕቢት በንቀት የምንጓዝ ከሆነ ህይወታችንን እንዳበላሸነው የልጆቻችንም ሆነ የልጅ ልጆቻችንን ህይወት አደጋ ላይ ነው የምንጥለው። ዛሬም አንዳንድ እኔን የመሰሉ ሰዎች አሁንም የኔን አይነት እርምጃ መውሰድ ሲገባቸው ፤ እነርሱ ግን አሁንም በፊት የአጠፉት አንሶዋቸው ሲራወጡ አያለሁ ። ምን ያህል ጨካኝነትስ ነው ዛሬ ደግሞ ለሌላ ጥፋት መዘጋጀት። ከኔ የበለጠ ሰይጣን ይኖራል ብዬ አለገምትም ነበር አሁን ግን እንዳለም አልጠራጠርም ።

የሰይጣን ቁራጭ ነኝ
የሰውን መጥፋት የምመኝ ።
እንዴት ሆኖ ከኔ ይኖራል
ይቅር ቢቀር ይሻላል።
ሁል ጊዜ የራሴን ትልቅነት የምመኝ
ማንንም እረግጬ ባልፍ የማያመኝ
እርጉም ነኝ እርጉም እኔን ተውኝ።
እርጉም ነኝ ፤ እርጉም ነኝ፡ እርጉም ነኝ።

የመጨረሻው ሰይጣን

ገና በልጅነቴ ነበር በተወለድኩበት ገጠር በጨካኝነቴ የታወቅሁት። በልጅነቴ ወንጭፍ ሰርቼ በድንጋይ ወፍ መግደል ከሁሉም የበለጠ ያስደስተኛል፡፡ ጭካኝነቴ አብሮኝ የተወለደ ስለሆን የሰፈሩ ሰው ሁሉ ይረግመኝ ነበር ። እርግማኑ ደርሶብኝ ነው መሰል እሄው አሁን በስተርጅና የራሴ ተግባር እራሴን እየተሚገተኝ የልብ እረፍት አሳጥቶ በጭንቀት ያኖረኛል።

እናቴ እኔ ስትወልድ ከምጥ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው የሞተችው።ትረፍ ያለኝ ስለሆነ ብቻ ነው የተረፍኩት።የእናት ፍቅር አላየሁም። ብዙም ሳይቆይ አባቴ ሌላ ሴት አገባና በእንጀራ እናት ማደግ ጀመርኩ። እንጀራ እናቴ እኔ ለእርሷ ብዙ ፍቅር ባይኖረኝም እሷ ግን መሃን ሰለነበረች እኔን እንደልጇ ታየኝ ነበር። እኔ ግን እንደናቴ ገዳይ ነው ሁልግዜ የማስባት። አንዳንድ ግዜ ውሃ አምጣ በምትለኝ ግዜ ውሃ ውስጥ ምራቄን እተፋበት ነበር።

እምንጬ ጋር የነበሩትን እንቁራሪቶች መግደል ከሁሉ የበለጠ ያስደስተኛል። እንቁራሪቶቹን ይገፎ ውሃ ሊቀዱ የመጡትን ሴቶችና ሕፃናትን ማሰፈራራት ደስታ ይሰጠኛል። ሁሉም ይህ እርጉም እናቱን የገደለ ስለሚሉኝ ከሰው ሁለ የተለየሁ እርጉም ፍጡር ሆኜ ነበር እራሴን የምቆጥርው ። ትንሽ አደግ ስል ሰክሮ በጨለማ የሚመጣ ሰው በድንጋይ መምታትና መደበቅ ጀመርኩ። ክፋት ሰርቼ የዋልኩ ዕለት እንቅልፍ በጥሩ ሁኔታ ይወስደኛል። አለበለዚያ ግን ነገ ምን አይነት ተንኮል እንደምሰራ ሳስብ ነበር የማድረው።

ይቀጥላል ።